የፍትህ ሚኒስቴር

# የመብቶች መግለጫ

በቁጥጥር ሰው ለዋለ የሚሰጥ
የተደራጀ ወንጀል እና አነስተኛ ወንጀል፤ ዕፅ ማዘዋወር እና ሽብርተኝነትን ሳይጨምር (የፈረንሳይ የወንጀል ህግ አንቀፅ 63-1, 706-73 እና 706-88)

**ይህ መረጃ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ ሊሰጡት ይገባል።**
**በህግ ጥላ ስር በሚቆዩበት ግዜ ሁሉ ይህ ዶክመንት ከእርስዎ ጋር ሊቆይ ይችላል።**

በህግ ጥላ ስር የሚገኙት በተደራጀ ወንጀል እና አነስተኛ ወንጀል ስር በእስር ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል ፈፅመዋል ወይም ለመፈፀም ሞክረዋል የሚል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጥርጣሬዎች በመኖራቸው ምክንያት መሆኑ ተነግሮዎታል።

ፈፅመዋል ተብለው ስለተጠረጠሩበት ወንጀል አይነት፣ ስለተፈጸመበት ቦታ እና ግዜ፣ እንዲሁም በቁጥጥር ስለዋሉበት ምክንያት የማወቅ መብት አሎት።

ስለነዚህ ነገሮች እስከ 24 ሰዓታት ሊቆይ በሚችለው በቁጥጥር ባሉበት ግዜ ውስጥ ይነገርዎታል።

ይህ ግዜ ሲያልቅ አቃቤ ህግ ወይም ጉዳዩን የሚያየው ዳኛ በቁጥጥር ስር የሚውሉበትን ግዜ ለተጨማሪ 24 ሰዓታት ሊያራዝመው ይችላል። ዳኛው ፈቃዱን ሊሰጥ የሚችለው ፊቱ ከቀረቡ ብቻ ነው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና የምርመራ ሂደቱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው፤ እያንዳንዳቸው 24 ሰዓታት የሚሆኑ ሁለት ተጨማሪ ማራዘሚያዎች በነጻነት እና እስር ዳኛ አልያም ጉዳዩን በሚመለከተው ዳኛ ሊሰጡ ይችላሉ።

ነገር ግን የመጀመሪያው 48 ሰዐት ሲያልቅ የሚከተሉት የምርመራ ሂደቶች ተገቢ ሆነው ከተገኙ፤ የነጻነት እና እስር ዳኛው በአቃቤ ህግ ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ዳኛ ጥያቄ መሰረት እስሩ አንዴ ብቻ እና ለ 48 ስዓታት እንዲራዘም ሊወስን ይችላል።

በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ ሲጠናቀቅ በአቃቤ ህግ ወይም ጉዳዩን በሚመለከተው ዳኛ ውሳኔ መሰረት ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ወይም ሊለቀቁ ይችላሉ። በመጀመሪያው ሁኔታ፤ ፍርድ ቤት የሚቀርቡት በተመሳሳይ ቀን ይሆናል። በግዛቱ ለዚሁ የሚሆኑ ቦታዎች ካሉ እና እስርዎ 72 ሰዐታት ካላለፈ፤ እስርዎ ካበቃበት አንስቶ 20 ሰዓታት በማይበልጥ ግዜ ውስጥ በሚቀጥለው ቀን ሊቀርቡ ይችላሉ። እስርዎ 72 ሰዓታት ካለፈ፤ ፍርድ ቤት የሚቀርቡት እስርዎ በሚያበቃበት ቀን ይሆናል።

## በተጨማሪም፤ የሚከተሉት መብቶች እንዳሎት ተነግሮዎታል፡-

### ለተወሰኑ ሰዎች ስለሁኔታው ማሳወቅ

አብሮት ለሚኖር ሰው፣ ከወላጅዎ ለአንዳቸው፣ ወይም ከወንድሞችዎ አልያም እህቶችዎ ለአንዳቸው በህግ ጥላ ስር ስላሉበት ሁኔታ በስልክ ማሳወቅ ይችላሉ።

ቀጣሪዎንም ማሳወቅ ይችላሉ።

የውጭ ዜጋ ከሆኑ፤ ለሀገርዎ ቆንጽላ ኃላፊዎች ማሳወቅ ይችላሉ።

ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ካልኖሩ በስተቀር እነዚህ ጥያቄዎችዎ ባነስዋቸው ከ 3 ሰዓት በማይበልጥ ግዜ ውስጥ ይስተናገዳሉ።

በህግ ከለላ ስር ያሉ ከሆነ፤ ሞግዚትዎ፣ ተገቢው አዋቂ ወይም ባላደራ ስለተወሰዱት እርምጃዎች እንዲያውቅ ይደረጋል።

ሆኖም ግን የማሳወቁ ሂደት መረጃን በመሰብሰብ ወይም በሰው ህይወት፣ ነፃነት ላይ አደጋን የሚፈጥር ከሆነ አቃቤ ህግ (ወይም ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ) ሊያዘገየው ወይም ሊያግደው ይችላል። እስርዎ ከ 48 ሰዓታት በላይ ከተራዘመ፤ በተመሳሳይ ምክንያት እስሩ መራዘሙን ለቤተሰብዎ ወይም ቀጣሪዎ የማሳወቁ ሂደት በነጻነት እና እስር ዳኛ (ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ዳኛ) ሊራዘም ይችላል።

### ከግለሰብ ጋር ስለመገናኘት

በህግ ቁጥጥር ስር እርስዎ እንደዋሉ ከተነገራቸው ሰዎች ከአንዳቸው ጋር በጽሁፍ፣ ስልክ ወይም ፊት ለፊት ለመገናኘት መጠየቅ ይችላሉ።

ጥያቄዎ በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ምክንያት ጋር አብሮ የማይሄድ ከሆነ፤ ወይም ወንጀል እንዲፈጸም መንገድ የሚከፍት ከሆነ መርማሪ ኦፊሰሩ ጥያቄዎን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል። የተጠቀሰው ኦፊሰር ወይም እሱ የሚሾመው ግለሰብ የሚያደርጉት ግንኙነት በእርሱ ቁጥጥር ስር፤ እንዲሁም በምን አይነት ሁኔታ እና ለምን ያህል ግዜ ከ 30 ደቂቃ በማይበልጥ መደረግ እንዳለበት ይወስናል።

የእስር ግዜዎ ከ 48 በላይ ከተራዘመ፤ መርማሪ ኦፊሰሩ ከቆንጽላ ኃላፊዎች ጋር የመገናኘት ጥያቄዎን ሊከለክል አይችልም።

## በዶክተር ስለመመርመር

በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ግዜ አንስቶ እስሩም በሚራዘምበት ግዜ በዶክተር ለመመርመር ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። የእስር ግዜዎ ከ 48 ሰዓት ካለፈ፤ በዶክተር የመመርመር ግዴታ ያለብዎት ሲሆን አዲስ የህክምና ምርመራ የመጠየቅ መብት እንዳሎትም ይነገሮታል።

በህግ ከለላ ስር ያሉ ከሆነ፤ ሞግዚትዎ፣ ተገቢው አዋቂ ወይም ባላደራ የህክምና ምርመራ እንዲደረግሎት ሊጠይቅ ይችላል።

## ቃል መስጠት፣ ጥያቄ መመለስ ወይም ዝም ማለት

ማንነትዎን ካረጋገጡ በኋላ፤ ክስዎ በሚካሄድበት ግዜ የሚከተሉት መብቶች አሎት፦

- ቃል መስጠት

- ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ መስጠት

- ወይም ዝም ማለት

## የጠበቃ ድጋፍ ስለማግኘት

### የጠበቃ ምርጫ

በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ግዜ አንስቶ፣ በክስ ሂደትዎ ግዜ፣ እና በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ በተራዘመበት በማንኛውም ግዜ ከመረጡት ጠበቃ ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ። ጠበቃ መቅጠር ካልቻሉ ወይም የመረጡት ጠበቃ ሊገኝ የማይችል ከሆነ ወዲያውኑ ጠበቃ እንዲመደብልዎ መጠየቅ ይችላሉ።

በተጨማሪም ጠበቃዎ ካገኟቸው ሰዎች መካከል በአንዳቸው ሊሾምልዎ ይችላል። ይህ በሚሆንበት ግዜ፤ የጠበቃውን መሾም ማረጋገጥ አለብዎት።

በህግ ከለላ ስር ያሉ ከሆነ፤ ሞግዚትዎ፣ ተገቢው አዋቂ ወይም ባላደራ ጠበቃ ሊሾም አልያም በህግ ባለሙያዎች ፕሬዝዳንት በኩል እንዲሾም ሊጠይቅ ይችላል።

### የህግ ድጋፍ

የውይይቱን ምስጢራዊነት በጠበቀ መልኩ ጠበቃዎ ለ 30 ደቂቃ ሊያገኝዎ ይችላል። በቁጥጥር ስር የሚውሉበት ግዜ ከተራዘመ፤ ጠበቃዎን በድጋሚ ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ።
በእርስዎ ጥያቄ መሰረት ጠበቃዎ እርስዎ የሚሳተፉባቸውን የክስ ሂደቶች፣ክርክሮች፣ምልልሶች ወይም ማንነትን የመለያ ውይይቶች ላይ መሳተፍ ይችላል።

### የምላሽ ግዜ

አፋጣኝ የችሎት ክስ ሂደት የሚፈልጉ የምርመራ ሂደቶች በሚያጋጥሙበት ግዜ፤ አቃቤ ህጉ አልያም ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ ጠበቃዎ እስኪመጣ ያለውን የ 2 ሰዐት ገደብ መጠበቅ ሳይጠበቅባቸው በፅሁፍ በሰፈረ እና ምክንያታዊ በሆነ ውሳኔ ችሎቱን ማስጀመር ይችላሉ።

አስገዳጅ ምክንያቶች ሲገኙም የጠበቃዎ ጠልቃ ገብነት ለ 48 ላልበለጠ ግዜ በአቃቤ ህጉ፤ የነጻነት እና እስር ዳኛው ወይም ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ ሊራዘም ይችላል።

## የትርጉም አገልግሎት ስለማግኘት

ፈረንሳይኛ የማይናገሩ ወይም የማይገባዎት ከሆነ ከክፍያ ነጻ በሆነ መልኩ በክስዎ ሂደትም ሆነ ከጠበቃዎ ጋር በሚነጋገሩበት ግዜ የትርጉም አገልግሎት የማግኘት መብት አሎት።

## ከእስር እንዲለቀቁ ስለመጠየቅ

በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ እንዲራዘም ሊወሰን ፍርድ ቤቱ በሚቀመጥበት ግዜ፤ ግዜው እንዳይራዘም እና ከእስር እንዲለቀቁ ያስችላል የሚሉትን ምክንያት ለጠቅላይ አቃቤ ህጉ ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው ዳኛ መንገር ይችላሉ።

## ከጉዳይዎ ጋር የሚገናኙ የተወሰኑ ነገሮችን የማግኘት መብት

በእርስዎ ወይም በጠበቃዎ ጥያቄ መሰረት እና በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ ከመራዘሙ በፊት የሚከተሉትን መጠየቅ ይችላሉ፦

- በቁጥጥር ስር መዋልዎን የሚገልፅ መግለጫ

- የመረመርዎ ዶክተር የሰጠው የህክምና ሰርቲፊኬት

- የክስ ሂደትዎ ቃለ-ጉባኤ

## አቃቤ ህጉን ስለማናገር

በቁጥጥር ከዋሉበት ግዜ አንድ አመት በኋላ መቀበልዎን በሚያረጋግጥ ድብዳቤ ወይም መቀበልዎን ለመዝገብ ቤት በማሳወቅ የክስዎን ፋይል ለማየት አቃቤ ህጉን መጠየቅ ይችላሉ።